# እንቢ በል ወገኔ

ጨዋ ትግስተኛ አዛኝና ሩህሩህ
ቁጥብ ሰው አክባሪ ተንኮል የሌለብህ
ለአለም የሚተረፍ መውደድና ፍቅርህ
ተትረፍርፎ ሞልቶ ለሰው ያለ ክብርህ::
ምስኪን ለፍቶ አዳሪ በላቡ ጠብታ
ጥሮ ግሮ ኗሪ አውታታ ከርታታ::
ለእለት ጉርሱ ብሎ ሲማስን ሲፈጋ
መደብ አንገፍግፎት ሲናፍቀው አልጋ
ሲማስን የሚውል መሽቶ እስከሚነጋ
ሲጣጣር የሚኖር አዲስ ቀን ፍለጋ::
ህይወቱን በሙሉ አፍሮ ተቆራምቶ
ለልጆቹ ሲኖር ራሱን ረስቶ
በላዩ ጣል አርጎ እራፊ ቡትቶ
የዛሬን ረስቶ የነገውን አይቶ::
እድሜ ልክ ስቃይ ዝንተ አለም ሰቆቃ
በችግር አለንጋ ሲገረፍ ሲወቃ
ተዘፍቆ እየኖረ በችግር አረንቋ::
ተፈጥሮ አጋድላበት ኑሮውን አክብዳ
በገዛ ሀገሩ ተቆጥሮ እንደባዳ::
በትብቱ መቃብር ባደገበት ቀዬ
አቀርቅሮ ዘሞ ዜማው ሆኖ እዬዬ::
ህይወት ተጣማበት ሆናበት ገዳዳ
ኢትዮጵያዊ መሆን ሀጢያት ሆኖ እዳ
እንባው እንደ ጅረት በጉንጩ ሲቀዳ
መውጫ መሰወሪያ ጠፍቶበት ቀዳዳ::
ይሄ አነሰ ብሎ ደሞ አል በቃ ብሎ
እግዜር የሰጠውን አምኖ ተቀብሎ
ኑሮን እንዳይገፋ ደፋ ቀና እያለ
ሌላ ችግር መጥቶ በላዩ ፏለለ::
ነጻነት የማያውቅ መጥቶበት ነጻ አውጪ

ታዛውን አቃጥሎ አሳደረው ውጪ::
ኢትዮጵያዊ ካባ ጃኖ ተከናንበው
እናውቅልሃለን እኛን ስማ ብለው
በችግር ላይ ችግር ስቃዩን ጨምረው
ዲሞክራሲ እያሉ ዲሞክራሲን ውጠው
ከፍጡር ሳይቆጥሩ አንገዋለው ጥለው::
ከደህና ወገንህ ሲያጣሉህ ሲያባሉህ
መርዝ እያጠቀሱ ሲግቱህ ሲያጎርሱህ
እንዳበድ ውሻ እያክለፈለፉህ
አናክሰው አባልተው አናጭተው ሊጥሉህ::
አንተን እያባሉ እያተናረኩ
ሴራ እየገመዱ በሳንጃ እያናኩ
እንደ ደህና ነገር ተንኮል እያኙኩ
ስጋህን ከታትፈው በደም እያቦኩ::
ያንን ጨርቃ ህጻን ልጅህን ባደባባይ
ደረቱን በጥርቀው በጠራራ ጸሃይ
የልፋትክን ውጤት አዝመራህን ሳታይ
ቀጥፈው እየጣሉ አውላላ ሜዳ ላይ::
ሌላ ምን ይመጣል ከዚህ የከረፋ
ልጅህ እበርህ ላይ ቀየህ ላይ ሲደፋ
እንደ ጭዳ ዶሮ ደሙ እየተንፏፏ
ግዳይ እንደጣለ ሲፏልል ሲያናፋ::
የሰው ልጅን ህይወት ከመጤፍ ሳይቆጥሩ
እንደ ናዚ ዘመን በካንፕ እያጎሩ
ስንቱን የተማረ ፍዳ እያስቆጠሩ
እነሱ በተድላ በደስታ ሲኖሩ
ከበሮ እየደቁ ጨቤ እየጨፈሩ::
ታዲያ እስከመቼ እንዲህ ትኖራለህ
በወገን ባላንጣ እየተሰቃየህ
አቀርቅሮ መሄድ ውርደት ሆኖ ምስህ
ኮሮጆህ ሳይሞላ ጠብ ሳይልልህ
ይሄ ነው ኑዛዜው ይሄ ኖሯል ውርስህ?

እምቢ በል ወገኜ አሻፈረኝ በለው
ከጫንቃዬ ውረድ ይበቃል ያለፈው
ጀርባዬ ሰርጉዷል ደምቷል ቦታም የለው
ትግስትም ዝምታም ወሰን ድንበር አለው
ምንድነው ፍራቻ እሱም ሰው እኛም ሰው::
መሪዎችህ ታስረው እለኝታ ልጆችህ
ላንተ መኖር ብለው ተባይ ሲመጥብህ::
መንገዱን ባሳዩህ እውነት ተፈልቅቃ
ጭቆናና በደል ሲቃይ እንዲበቃ
በነሱ መስዋእት ለድል እንደትበቃ
እንቢበል ይሉሃል የግፍ ስርአት ይብቃ::
የትግላችን ቀንዲል ችቦ ተለኩሷል
ብርሃን ውጋጋኑ ዳር ከዳር ፈንጥቋል
የቅንጅት መንፈስ በውስጣችን ናኝቷል
መሪ ውጋጋኑ ለድል ያበቃናል::
እንደዚህ ከመኖር እየታየ ፍዳ
ተነቃነቅና ያበጠው ይፈንዳ
የክብር የነጻነት ሰላለብህ እዳ
የጭቆናን መንበር ከላይህ ላይ አጽዳ::
እምቢ በል ወገኜ ዝምታው ምንድነው
ፍራቻን ማን ጠራው እሱም ሰው እኛም ሰው
በጉልበት መጣ እንጂ እግዚአብሄር አልቀባው::
ወይ ሁለት ጊዜ ሺ ዘመን አይኖር
ዳግም ተምልሶ ለማድረግ ድርድር
ሁሌ እየጨሱ ተቃጥሎ ከማረር
ይሄው ምርጫው ቀርቧል መኖር አለመኖር::
ሲረግጡህ ሲያቦኩህ እንደልስን ጭቃ
የሚያተራምሱህ ብሏቸው አልበቃ
ምንያመጣል ብለው ሲመጻደቁብህ
ይህየው ዛሬ ደግሞ አጉራ ዘለል አሉህ
ተናቅህ ተዋረድህ ሰደቡህ ዘለፉህ
የምትጠብቀው ሌላ የቀረ አለህ?

አግድም አደግ ብቃይ አራሙቻ ሁላ
ዛሬ ጊዜ ሰጥቶት ባንተላይ ቢያክላላ::
የተነቃነቀ የበሰበሰ ጥርስ
መነቀሉ ላየቀር ቀነ ጊዜው ሲደርስ
ቢበየድ ቢሰራ ቢቀቡት ቢኩሉት
ውስጡ ተቦርቡሯል የለውም መሰረት::
እምቢ በል ወገኔ ሆ ብለህ ተነሳ
የወንዜው ጉምጉም የወንዜው ሳቢሳ::
ሆ ብለህ ተነሳ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ
አሳየው ክንድህን የምሬትን ጅራፍ
ለወሳኙ ትግል ተዘጋጅ ተሰልፍ
ለምዬ ኢትዮድያ ተወጋ ተሰየፍ
ጥሩ ቀን አይመጣም መጥፎ ጊዜ ሳያልፍ::

ከ..ዘዬ